DEPARTMENT OF HEALTH

# ነፍሰጡር ለሆኑ ሰዎች የሄፓታይቲስ B መረጃ

## ሄፓታይቲስ B ምንድን ነው?

- ሄፓታይቲስ B በቫይረስ የሚከሰት የጉበት በሽታ ነው። በሄፓታይቲስ B የተያዙ ብዙ ሰዎች ላይ ቫይረ፥ የህይወት ዘመን ህመም በማስከተል፣ በሰውነታቸው ውስጥ ይቆያል።
- ሄፓታይቲስ B የጉበት ጉዳት፣ የጉበት ድካም፣ እና የጉበት ካንሰርን ጨምሮ በጊዜ ሂደት ከባድ የጤና ችግሮችን ያስከትላል።
- ሄፓታይቲስ B ያለባቸው አብዛኞቹ ሰዎች ምልክቶች የላቸውም እንዲሁም እንዳለባቸው ራሱ ላያውቁ ይችላሉ፣ ነገር ግን ወደ ሌሎች ሰዎች ማስተላለፍ ይችላሉ።
- ነፍሰጡር ሰዎች በእያንዳንዱ እርግዝና ወቅት የሄፓታይቲስ B ምርመራ ማድረግ አለባቸው።

## ነፍሰጡር ሰዎች ምርመራ ማድረግ ያለባቸው ለምንድን ነው?

- ነፍሰጡር ሰዎች የሄፓታይቲስ B ፖዘቲቭ ምርመራ ካላቸው፣ ልጃቸው በወሊድ ወቅት ህክምና ማግኘት አለበት። በሚወለዱበት ጊዜ ህክምና የሚያገኙ ህጻናት በሄፓታይቲስ B እምብዛም አይያዙም።
- ህጻናት በሄፓታይቲስ B ኢንፌክሽን በሚያዙበት ጊዜ፣ በህይወት ዘመን ኢንፌክሽን የመሆን ዕድሉ ከፍተኛ ነው።

## ሄፓታይቲስ B ቢኖርብዎት እና ነፍሰጡር ቢሆኑ ምን ያደርጋሉ?

- የሄፓታይቲስ B ኢንፌክሽንዎን እንዴት መቆጣጠር እንደሚችሉ ለመወያየት የጤና እንክብካቤ አቅራቢዎን ይጎብኙ።
- ሄፓታይቲስ B ን ወደ ልጅዎ የማስተላለፍ ዕድልዎን መቀነስ የሚችሉ ህክምናዎች አሉ።

## ልጅዎን በበሽታው ከመያዝ እንዴት ሊጠብቁት ይችላሉ?

- ሄፓታይቲስ B እንዳለብዎት የማያውቁ ከሆነ፣ የሄፓታይቲስ B የደም ምርመራ እንዲያዝልዎት አቅራቢዎን ይጠይቁ።
- የሄፓታይቲስ B ምርመራዎ ኔጌቲቭ ከሆነ፣ ስለ ሄፓታይቲስ B ክትባት አቅራቢዎን ይጠይቁ።
- የሄፓታይቲስ B ምርመራዎ ፖዘቲቭ ከሆነ፣ ልጅዎ ህክምና እና ክትትል ያስፈልገዋ፦
  - ልጅዎ ከወሊድ በኋላ የክትባት ዙሩን የመጀመሪያ ዶዝ እንዲሁም hepatitis B immune globulin (HBIG፣ ሄፓታይቲስ B ኢሚዩኖ ግሎቢሊን) ን ይወስዳል።
  - ልጅዎ የሄፓታይቲስ B ክትባት ዙሩን መጨረስ አለበት።
  - ከክትባቱ ዙር በኋላ፣ ልጅዎ ከሄፓታይቲስ B መጠበቁን እርግጠኛ ለመሆን ሐኪምዎ ደም ይወስዳል።
- ሄፓታይቲስ B ቢኖርብዎትም እንኳን ጡት ማጥባት አስተማማኝ ነው።



Minnesota Department of Health
Perinatal Hepatitis B Program
PO Box 64975
St. Paul, MN 55164-0975
651-201-5414, 1-877-676-5414
www.health.state.mn.us/hepatitis

01/31/2023

*ይህን መረጃ በተለየ ቅርፀት ለማግኘት፣ በሚከተለው ይደውሉ፦ 651-201-5414።*